# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**በቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ የጾምና የጸሎት ፕሮግራም**

**መቼ፡**-June 19th to 21st

**ሰአት፡** 7:00 to8:30pm

**መስመር፡** 712-451-0282፤ Acc 18-25-04

**መመሪያ ጥቅሶች፡** ዮሐ. 12:16፤ ሉቃስ 11:13

**በችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የተዘጋጀ የፒክኒክ ፕሮግራም**

በ June22, 2019 (በ12 p.m. Noon) በችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት የተዘጋጀ የፒክኒክ ፕሮግራም ስለሚኖረን ሁላችንም ለመገናኘት ጊዜአችንን እንድናመቻች እናሳስባለን። ይህ ፕሮግራም ታላቅ የሕብረት ጊዜ እንደሚሆንልን እናስባለን።

- ታጣፊ ወንበሮች ያለን ይዘን እንምጣ
- ድንኳን ያለን ይዘን እንምጣ
- ኳሶችና መጫወቻወች ያለን ይዘን እንምጣ
- ከፕሮግራሙ በፊትና ለመርዳት የምችል ሁሉ እናግዝ
- ትኩስ ምግም እንድናገኝ በሰአቱ እንገኝ

**በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት**

አንዳንድ ማሳሰቢያዎች:

- ከችካጎ የምንለቀው July 4 at 10 a.m. ይሆናል::
- ቦታው በ 1p.m. ለመድረስ እናስብለን::
- አድራሻ: W2511 WI-23, Green Lake, WI 54941
- ሁላችንም በየራሳችን መኪና እንመጣለን::
- ትራንስፓርት የምትፈልጉ አስታውቁን::
- መጫወቻወች እንደ ኳስ የመሳሰሉ ይዛችሁ ለመምጣት የምትችሉ ለእህት ዲቦራ አስታውቁ::



⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሸማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10



"... የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ ..."
(ዮሐ. 2:5)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.

**June 16, 2019**

**ሰኔ 9፤ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | ወንድም መኮንን ጂኔሎ |
| አምልኮ....................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| ቃል ............. | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

## <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።” (1ጴጥ. 5:7)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ

በዮሐንስ ምእራፍ ሁለት ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀምርያውን ምልክት ሲያደርግ እናነባለን። አውዱ የሰርግ ሥነ-ስርአት ነው። ቦታው በገሊላ አውራጃ ቃና በምትባል ከተማ ነው። በዚህ ሰርግ ላይ ጌታችንና ደቀ መዛሙርቱ እንዲሁም እናቱ ቅድስት ማርያም ታድመዋል። በባህላችን እንደሚደረገው ሁሉ በአይሁድ ባህልም ሰርግ ደግሶ መዳር፤ እንግዶችን ጋብዞ ማብላት የተለመደ ነው። በዚህ ሰርግ ላይ ሽር ጉድ እያሉ የሚያስተናብሩ አገልጋዮች አሉ። መለስ ቀለስ እያሉ የጎደለውን ይሞላሉ፣ ከማጀት ወደ እልፍኝ፤ ከእልፍኝ ወደ ማጀት ተፍ ተፍ እያሉ ታዳሚውን ያስተናግዳሉ። ደግሞም በሰርጉ የከበሩ ሰዎችም ታድመዋል። የከተማው አስተዳዳሪ (ከንቲባ) በዚያ አለ። ታዳሚው ብዙ ይመስላል። ደግሞም ደጋሾች አሉ። “ብሉ እንጂ፣ ጠጡ እንጂ” እያሉ ፈካ ብለው በታዳሚው መካከል ይመላለሳሉ። በዚህ መኃል ነው እንግዲህ የደጋሾቹ ወይን ጠጅ አለቀ የሚለው አስደንጋጭና አሳፋሪ ነገር ብቅ ያለው። በዚህ ችግር ወቅት እናቱ ቅድስት ማሪያም ካደረገችው ነገር ብዙ ቁም ነገሮችን እንማራለን።

አንደኛ እናቱ ቅድስት ማርያም ችግሩን ወደ ጌታ ወሰደችው። ቅድስት ማርያም የወይን ጠጁ ማለቁን በሰማች ጊዜ ችግሩን እያሰላሰለች አልተቀመጠችም። ወይንም በችግሩ ግራ ተጋብታ እምታደርገው አልጠፋትም። ይልቁንም የችግሩ መፍተሄ እንዳለው በልቧ ወዳመነችው ወደ ጌታ ኢየሱስ አመጣችው። “የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም” አለችው። ወገኖቼ ይህ ትልቅ ማስተዋል ነው። የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሙን ምንድነው የምናደርገው? ለችግሩ መፍተሄ ለማግኘት ወደ ማን ነው የምንሄደው? ከጌታ እናት ከቅድስት ማርያም የምንማረው አንዱ ትልቁ ነገር ማንኛውም ችግር ሲገጥመን መፍተሄ በጁ ወዳለው ጌታ ይዘነው እንቅረብ። አንድም ችግሩን ከፊታችን ያነሳዋል አለያም በችግሩን የምናልፍበትን ጸጋ ይሰጠናል።

ሁለተኛ እናቱ ቅድስት ማርያም በድግሱ ስፍራ ለነበሩት አገልጋዮች “የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ” የሚልን ምክር ሰጠቻቸው። ይህ ግሩም፣ በማስተዋል የተሞላ አስደናቂ ምክር ነው። እርሱ የሚላችሁን አንዱንም ሳታስቀሩ አድርጉ። ምናልባት የሚላችሁ አሁን ላይገባችሁ ይችላል ነገር ግን አድርጉት። ቅድስት ማርያም ጌታ የሚለውን በማድረግ ውስጥ የችግሩ መፍተሔ እንዳለ አስተውላለች። ወገኞቼ:- ዛሬም እኛ ጌታ በቃሉና በመንፈሱ የሚለንን ሁሉ ብናደርግ መፍተሔ እናገኛለን። በቃሉ ውስጥ የጌታ ድምጽ አለ። በቃሉ ውስጥ ፈውስ አለ። በቃሉ ውስጥ ምክር አለ። በቃሉ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይሰራል። ቃሉን ስንታዘዝ መከናወን እናገኛለን።

በሶስተኛ ደረጃ ከዚህ ክፍል የምንማረው የገጠመንን ማናቸው ነገር ይዘን ወደ ጌታ ስንቀርብ ከሁኔታው ጌታ የሚከብርበት የከበረና የላቀ ነገር ይወጣል። ቅድስት ማርያም የደጋሾቹን ችግር መፍተሄ ወዳለው ጌታ አመጣችው። እርሱም ደግም ትእዛዝ ሰጠ። አገልጋዮቹም የሚላቸውን አደረጉ። ውጤቱ አስደናቂ ነበር። የሆነው ነገር የችግሩ መቃለል ብቻ ሳይሆን ከዛ ችግር የከበረ ነገር ወጣ። የሚበልጥ ጣእም ያለው የወይን ጠጅ ወጣ። ጌታ የከበረበት ነገር ወጣ። ወገኖቼ:- በእኛም ህይወት እንዲሁ ነው። አለቀ፣ አበቃ ያልነውን ነገር ወደ ጌታ ይዘነው ስንቀርብ ለመደነቂያ የሚሆንን ነገር ጌታ ከዛ ነገር ውስጥ ያወጣል። በምንም ሁኔታ ተስፋ አትቁረጡ ነገር ግን የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ ወደ ጌታ አምጥታችሁ በግሩ ስር ጣሉት። መፍተሔ ከጌታ ዘንድ ይወጣል። ክብር ሁሉ ለጌታ ይሁን። አሜን!